# የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ

ለእያንዳንዱ ልጅ ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት ለማቅረብ የቆመ ነው



Brenda L. Wolff ብረንዳ ኤል. ዎልፍ
President ፕሬዚደንት
ዲስትሪክት 5



Karla Silvestre ካርላ ሲልቬስትር
Vice President ም/ፕሬዚደንት
አት-ላርጅ/At-Large



Judith R. Docca ጁዲት አር. ዶካ
ዲስትሪክት 1



Shebra L. Evans ሼራ ኤል. ኤቫንስ
ዲስትሪክት 4



Lynne Harris ልይን ሃሪስ
አት-ላርጅ/At-Large



Patricia B. O'Neill
ፓትሪሽያ ቢ. ኦ'ኔይል
ዲስትሪክት 3



Rebecca K. Smondrowski
ረቤካ ኬይ. ስሞንድሮውስኪ
ዲስትሪክት 2



Nicholas (Nick) Asante
ኒኮላስ (ኒክ) አሳንቴ
ተማሪ አባል



Jack R. Smith, Ph.D.
ጃክ አር. ስሚዝ (ዶ/ር)
Superintendent of Schools
የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት

## ስለ እኛ እና እንዴት ልንረዳችሁ እንደምንችል ማስገንዘቢያ

የሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ በካውንቲው ኦፊሲየላዊ የትምህርት መመሪያ አፍላቂ አካል ነው። ቦርዱ የህዝባዊ ትምህርት ስርኣት አቅጣጫና አመራር/አፈጻጸም ሀላፊ ነው። ተልዕኳችን በማደግ ላይ ያለውንና ባለ ብዙ ስብጥር የተማሪ ማህበረሰብን ተጠቃሚ ለማድረግ በማህበረሰብ የተደገፉ ግቦች፣ ከመመርያዎች፣ እና ከሪሶርስ ጋር ከፍተኛ ጥራት ያለው የትምህርት ስርአት የአመራርና ቁጥጥር ብቃት ለመስጠት ነው።

ቦርዱ የሚያካትተው ለአራት አመት የጊዜ ገደብ በመራጮች የተመረጡ ሰባት የካውንቲ ተቀማጮችንና ለአንድ አመት የጊዜ ገደብ በሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የተመረጠ(ች) አንድ ተማሪን ነው። የቦርድ አባሎች የሚመረጡት በካውንቲ አቀፍ ነው ነገር ግን ለምርጫ የሚቀርቡት ከየአቅጣጫው፣ ወይም ከመኖርያቸው የቦርድ ዲስትሪክት ነው።

ራዕያችን፡- ለእያንዳንዱና ለማንኛውም ተማሪ እጅግ የላቀ ህዝባዊ ትምህርት በማቅረብ ትምህርት እንዲሰርፅ እናደርጋለን።

በዚች መፅሄት፣ ስለ ትምህርት ቦርድ ሚናዎችና ሃላፊነቶች፣ በህዝባዊ ትምህርት እንዴት ተሳታፊ መሆን እንደሚቻል፣ እና ለእርስዎና ለልጆችዎ እንዴት አገልግሎት መስጠት እንደምንችል ልናሳውቃችሁ እንፈልጋለን።

The Montgomery County Board of Education, 850 Hungerford Drive, Suite 123, Rockville, Maryland 20850; ስልክ፦ 240-740-3030; Fax: 301-279-3860፤ ኢ-ሜይል BOE@mcpsmd.org; ድረ-ገጽ፦ www.montgomeryschoolsmd.org/boe/

## ቋሚ ኮሚቴዎች፡-

አምስት የቦርድ ቋሚ ኮሚቴዎች አሉ። ኮሚቴዎቹና አባሎቻቸው የሚከተሉት ናቸው፡-

### የኮሚኒኬሽን እና ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ውስጥ ስለ ኮሙኒኬሽን እና ተሳትፎ ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ሰፊ የሐሳብ ልውውጥ የማድረግ መስተጋብሮችን ያከናውናል።

Shebra L. Evans (Chair)
ሼብራ ኤል. ኢቫንስ (ሊቀመንበር)
Nicholas Asante ኒኮላስ አሳንቴ
Karla Silvestre ካርላ ሲልቨስትር
Rebecca K. Smondrowski
ረቤካ ኬይ. ስሞንድሮውስኪ

### የፋይናንስ አስተዳደር፡-

የሞንጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ፋይናንስ፣ ካፒታል፣ እና የሰው ኃይል፣ የቦርዱን መንቀሳቀሻ በጀትን ጨምሮ፣ የካፒታል ማሻሻያዎች ፕሮግራም፣ የሰራተኛ ቅጥርና እድገት ፕሮግራሞች፣ እና የገንዘብ ምደባዎችን አስተዳደርና ኦዲትን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ዳግም እይታ ያደርግባቸዋል።

Lynne Harris (Chair)
ልእይን ሃሪስ (ሊቀመንበር)
Judith R. Docca ጁዲት አር. ዶካ
Patricia B. O'Neill ፓትሪሺያ ቢ. ኦ'ኔይል

### የፖሊሲ አስተዳደር

ከበላይ ተቆጣጣሪውና ከሰራተኞች ጋር በመሆን ለሙሉው ቦርድ የሚቀርብ ረቂቅ መመርያ ያዘጋጃል/ያዳብራል።

Patricia O'Neill (Chair)
ፓትሪሺያ ቢ. ኦ'ኔይል (ሊቀመንበር)
Nicholas Asante ኒኮላስ አሳንቴ
Judith R. Docca ጁዲት አር. ዶካ
Rebecca K. Smondrowski
ረቤካ ኬይ. ስሞንድሮውስኪ

### ልዩ ትኩረት የሚሰጣቸው ማህበረሰቦች

ልዩ የትምህርት አገልግሎቶች፣ የባለ ተስጥኦና የላቀ ችሎታ ትምህርት፣ አማራጭ ፕሮግራሞች፣ የ ESOL አገልግሎቶች፣ እና የባለበርካታ ቋንቋ ድጋፍ የሚያስፈልጓቸው የልዩ ህዝቦችን ፍላጎቶች ለማሟላት የተተለሙ ጉዳዮችና የትምህርት ፕሮግራሞች ላይ ዳግመ-እይታ ያደርግባቸዋል።

Rebecca K. Smondrowski (Chair)
ሬቤካ ኬይ. ስሞንድሮውስኪ (ሊቀመንበር)
Judith R. Docca ጁዲት አር. ዶካ
Karla Silvestre ካርላ ሲልቨስትር

### ስልታዊ የፕላን ዝግጅት (Strategic Planning)

የት/ቤት ስርአትን የረጅም ጊዜ አቅጣጫ ለማገናዘብ መድረክ ይሰጣል፤ የረጅም ጊዜ ፕላን ዝግጅት አቀራረብን ይገመግማል፤ እና ስልታዊ የፕላን ሀሳቦችን ለቦርዱ ያቀርባል።

Karla Silvestre (Chair)
ካርላ ሲልቨስትረ (ሊቀመንበር)
Lynne Harris ልይን ሃሪስ
Shebra L. Evans ሼራ ኤል. ኤቫንስ

## Advisory Committees
## አማካሪ ኮሚቴዎች

ቦርዱ በተጨማሪ የሚከተሉት አማካሪ ኮሚቴዎች አሉት፡ - Ethics Panel, Collaboration Board for Career and Technology Education, and the District Committee on Assessments.

## የስብሰባ ጊዜያት

የኮሚቴ ስብሰባዎች በትምርት ቦርድ ድርጣብያ ይለጠፋል። www.montgomeryschoolsmd.org/boe. ህዝቡ የኮሚቴ ስብሰባዎች መከታተል ይችላል በውይይቶቹ ግን ላይሳተፍ ይችላል።

## የቦርድ ሚናዎችና ሃላፊነቶች

የትምህርት ቦርድ ስልጣኖችና  የተግባር ግዴታዎቹ በEducation Article of the Annotated Code of Maryland/በሜሪላንድ አኖቴትድ ኮድ የትምህርት አንቀፅ እና Title 13A የሜሪላንድ ደንቦች ኮድ/Code of Maryland Regulations ተብራርተዋል/ተገልጸዋል። የቦርዱ ተቀዳሚ ሃላፊነቶች፣ የት/ቤት ስርአት ስልታዊ ፕላን ለመደገፍ የተቀናጁት፣ የሚከተሉትን፣ በነሱ ሳይወሰኑ፣ የሚያካትቱ ናቸው፡-

1. የት/ቤቶችን የበላይ ተቆጣጣሪ መምረጥና መሾም።
2. መመሪያዎችን ማዘጋጀት እና መተርጎም።
3. የካፒታልና የስራ ማስኬጃ በጀቶችን ማፅደቅ።
4. ትምህርታዊ፣ የበጀት፣ የመገልገያ፣ እና የፋይናንስ ጉዳዮች (ህጋዊ ስምምነቶችን ማፅደቅ ጨምሮ) ውሳኔዎች መስጠት።
5. የስርአተ ትምህርት መመሪያዎችና የጥናት ኮርሶችን መመስረት።
6. የት/ቤት ስርአትን የትምህርትና የአስተዳደር አመራር ቀጣይ ግምገማ ማካሄድ።
7. የት/ቤት ክልሎችን/ወሰኖችን መወሰን።
8. ከዜጎች፣ ሰራተኞች፣ እና ተማሪዎች ጋር መገናኘት።
9. በተለይ ይግባኞችን በመወሰን እንደ ዳኛ ሆኖ መስራት።
10. የህግ ነክ አጀንዳ ማራመድ።
11. ሰራተኞች መመደብ/መሾም።

## የቦርዱ ሚናዎችና ሃላፊነቶች ከበላይ ተቆጣጣሪው እንዴት ይለያሉ?

- ቦርዱ መመርያዎችን ያስቀምጣል እናም የበላይ ተቆጣጣሪው መመርያዎቹን ይተረጉማል ይተገብራልም።
- የበላይ ተቆጣጣሪው የካፒታልና የስራ ማስኬጃ በጀቶችን ሃሳብ ያቀርባል፣ ነገር ግን ለካውንቲው ምክር ቤትና ለካውንቲ ስራ አስፈፃሚ የሚቀርቡትን በጀቶች ቦርዱ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል።
- አንድ ወላጅ ይግባኝ ካለ፣ በበላይ ተቆጣጣሪ የተወሰዱትን ውሳኔዎች ቦርዱ ይገመግማል።
- ቦርዱ ሰራተኞች ይመድባል/ይሾማል። የበላይ ተቆጣጣሪ ሰራተኞች ይመድባል የሙያቸውን እድገት/መሻሻል ይንከባከባል።
- ቦርዱ የንብረቶችን ባለቤትነት በስሙ ይጠብቃል ለአገግሎቶችም ውል ይገባል። የበላይ ተቆጣጣሪው በውሉ መሰረት የፍጆታ ዕቃዎችና የአገልግሎቶች አቅርቦት ይቆጣጣራል።

## የቦርድ ስብሰባዎችና ተሳትፎ

በአብዛኛው ቦርዱ በወር ሁለት የስራ ስብሰባዎችን ያካሂዳል። የሙሉ-ቀን የስራ ስብሰባ አብዛኛውን ጊዜ በወሩ ሁለተኛ ማክሰኞ ይካሄዳል፣ የምሽት የስራ ስብሰባ የሚካሄደው የሙሉ-ቀኑን ስብሰባ ተከትሎ በሚመጣው ሁለተኛው ሰኞ ነው።

እነዚህ ስብሰባዎች በአብዛኛው የሚከናወኑት በ Carver Educational Services Center, Rockville, Maryland ነው። የስብሰባ አጀንዳ እና ቁሳቁሶች በቦርዱ ድረ-ገጽ ላይ ይለጠፋሉ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/boe/meetings/index.aspx#calendar።

አስተያየት ለማቅረብ ፍላጎት ያላቸው ግለሰቦች በሚከተለው ድረ-ገጽ ላይ መመዝገብ ይችላሉ።www.montgomeryschoolsmd.org/boe/community/participation.aspx

ቅጹን/ፎርሙን በአጠቃላይ ከስብሰባ በፊት ካለው ዓርብ 9:00 a.m. ጀምሮ እስከ ለስብሰባ ቀጠሮ ከተያዘበት ሰኞ ቀን 9:00 a.m. ድረስ ማግኘት ይቻላል። በስብሰባው ቀን ተገቢውን ወረቀት በመፈረም ለተናጋሪዎች ሊገኙ የሚችሉ ቦታዎችን የቦርድ ስብሰባ ከመጀመሩ 15 ደቂቃዎች አስቀድሞ ለህዝብ የተዘጋጀዉ ከመካሄዱ በፊት ማስያዝ ይቻላል አስተያየቶች። ተናጋሪዎች ምስክርነቶቻቸውን በቅድሚያ በኢ-ሜይል እንዲልኩ እናበረታታለን boetestimony@mcpsmd.org፣ በዚህ ቁጥር 301-279-3860 ፋክስ ያድርጉ፣ ወይም ለትምህርት ቦርድ ጽ/ቤት ያቅርቡ።

ከልዩ የዝባዊ ሀሳብ መስጫ መድረኮች በተጨማሪ፣ ቦርዱ ስለ የስራ ማስኬጃ በጀት፣ ካፒታል በጀት፣ እና የት/ቤት ክልሎች አመታዊ የሀሳብ መቀበያ/መስጫ መድረኮችን ያካሂዳል።

የነዚህ ህዝባዊ ሀሳብ መስጫ መድረኮች አጠቃላይ መመሪያዎች እንደሚከተሉት ናቸው፡-

1. በተቻለ ወቅት፣ ህዝባዊ ችሎት ከአንድ ወር በፊት አስቀድሞ ፕሮግራም ይደረጋል።
2. እባክዎ ይህንን የቦርዱን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡-www.montgomeryschoolsmd.org/boe/community/participation.aspx በድረ-ገጽ ለመመዝገብ እና የሸንጎ ማስታወቂያዎች የበለጠ ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት።

## የበጀት ሂደት

ቦርዱ በያንዳንዱ ዓመት የትምህርት ስርአቱን ስራ ማስኬጃ በጀትና ካፒታል በጀት መገምገምና ማፅደቅ አለበት።

### ካፒታል በጀት

**ጁን 1 ሲደርስ**
የክላስተር ተወካዮች ያቀረቧቸውን መፍትሄዎች፣ ቅደም ተከተሎች፣ ወይም ክላስተሩ ለት/ቤቶች የለያቸውን ስጋቶች ለበላይ ተቆጣጣሪው ይልካሉ።

**የኦክቶበር ወር መጀመርያ ላይ**
የበላይ ተቆጣጣሪው የምዝገባ ሂደቶችን እና የመገልገያዎች ፕላን ጉዳዮችን ለመገምገም ከቦርዱ ጋር ህዝባዊ የስራ ጊዜ ያካሂዳል።

**ኦክቶበር-አጋማሽ**
የበላይ ተቆጣጣሪው ባለፈው ስፕሪንግ ስለተከናወኑ የወሰን ጥናቶች እና ወይም የፕላን ጥናቶች የቀረቡ ሃሳቦችን ይፋ ያደርጋል።

**ኖቬምበር መጀመሪያ ላይ**
የት/ቤቶች ዋና የበላይ ተቆጣጣሪ የስድስት ዓመት የካፒታል ማበልጸጊያ ፕሮግራም (CIP) ንድፍ ወይም ማሻሻያዎችን እና የአንድ ዓመት ካፒታል ባጀት በህትመት ያቀርባል/ይፋ ያደርጋል።

**ኖቨምበር**
ቦርዱ ለክልሎች ወሰን ለውጦች አማራጭ መፍትሄዎች አባሎቹ ሊያቀርቡ የሚችሉበት የስራ ክፍለ ጊዜ ያካሂዳል። ኖቬምበር ከማለቁ በፊት ውሳኔዎች እንዲወሰዱ ፕሮግራም በማድረግ፣ ቦርዱ ስለ መገልገያዎችና የክልሎች ወሰን የውሳኔ ሀሳቦች ህዝባዊ ስብሰባዎችንም ያካሂዳል።

**ዲሴምበር-ጀኑዋሪ**
የካውንቲው ስራ አስፈፃሚ የቦርዱን CIP ጥያቄ ይገመግምና ለካውንቲው ምክር ቤት የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል።

**ፌብሩዋሪ-ሜይ**
የካውንቲው ምክርቤት የተጠየቀውን CIP ይገመግማል።

ስፕሪንግ
የበላይ ተቆጣጣሪው ለዊንተር የድንበር/ክልል ጥናቶችና ለተሸጋገሩ ጉድዮች (ካሉ) የውሳኔ ሃሳቦችን ይፋ ያደርጋል። ቦርዱ ስለዊንተር የወሰን ጥናቶች (ካሉ) የቀረቡ ሀሳቦች እርምጃ ከመውሰዱ በፊት የስራ ክፍለ-ጊዜዎችና ችሎቶች ያካሂዳል።

ሜይ
የካውንቲው ምክር ቤት CIP እና ካፒታል በጀቱን ያፀድቃል።

*ማሳሰቢያ፡- ዲሴምበር-ሜይ መጀመርያ—የስቴት CIP በሚመለከት ሸንጎዎችና ውሳኔዎች ይከናወናሉ።

## የስራ ማስኬጃ በጀት

ዲሴምበር
የበላይ ተቆጣጣሪው በጀቱን እንዲቀበሉ ለቦርድ አባሎች የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል።

ጃንዋሪ
በበላይ ተቆጣጣሪው የውሳኔ ሃሳቦችና ቦርዱ በራሱ በሚያገናዝባቸው ጉዳዮች ተጨማሪ መረጃዎች ለማግኘት ቦርዱ ችሎቶችና የስራ ክፍለጊዜዎች ያካሂዳል።

ማርች 1
በየአመቱ በዚህ እለት ቦርዱ በጀቱን መቀበልና ለካውንቲው ስራ አስፈፃሚና ለካውንቲ ምክር ቤት ገቢ ማድረግ አለበት።

ጁን 1
የካውንቲው ምክር ቤት በትምህርት ስርአት በጀት ውስጥ ለእያንዳንዱ በየፈርጁ የስቴት የገንዘብ ድርሻ መወሰን አለበት።

ጁን
የካውንቲው ምክር ቤት የወሰደውን እርምጃ ለማክበር እና ስለወጭ ተቀዳሚዎች የቦርዱን የመጨረሻ ውሳኔ ለማንፀባረቅ ቦርዱ በበጀቱ ላይ ማስተካከያዎችን ያደርጋል።

ጁላይ 1
የት/ቤት ስርአት አዲሱ የስራ ማስኬጃ በጀት ተግባራዊ ይሆናል።

# የእንባ ጠባቂ—የቦርድ ጽ/ቤት እንዴት ሊያግዝዎ እንደሚችል

እንባ ጠባቂ የሚሾመው በሞንትጎመሪ ካውንቲ (Montgomery County) የትምህርት ቦርድ ነው እናም፣ በተለይ ኦፊስየላዊ መፍትሄ ለኖራቸው ለማይችል፣ ከት/ቤት-የተያያዙ ችግሮች በተቻለ መጠን በፍጥነትና በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመፍታት የሚሻ ተፅእኖ የሌለበት/ነፃ ወይም ገለልተኛ የሆነ ወገን ነው።

አቤቱታ ሰሚው(ዋ)/እንባ ጠባቂው/ዋ፣ እርስዎ ከፈቀዱ፣ ሁሉንም ሠነዶች ለማየት ስልጣን አለው/አላት። ሁሉም የት/ቤት ስርአት ሰራተኞች ከእንባ ጠባቂው/አቤቱታ ሰሚው(ዋ) ጋር እንዲተባበሩ መመርያ ደርሷቸዋል።

ምንም እንኳን እንባ ጠባቂው ኦፊሴላዊ ይግባኞችን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ለመመለስ ዝግጁ ቢሆንም፣ በእንደዚህ አይነቶቹ ጉዳዮች አቤቱታ ሰሚው(ዋ)/እንባ ጣባቂው/ዋ በአብዛኛው ጣልቃ አይገባም/አትገባም።

እንባ ጠባቂውን በ 240-740-3030 መገናኘት ይችላሉ።

Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
ህትመት በ Department of Materials Management for the Board of Education
ትርጉም፡- የቋንቋ ድጋፍ አገልግሎት ክፍል • የኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት
Language Assistance Services Unit • Office of Communications
0278.21ct • Editorial, Graphics & Publishing Services • 12/20 • NP